# ከወንጌል ጥቂት

መስከረም 1998

September 2005



አምላካችን መጠጊያችንና ኃይላችን ፥

ባገኘን በታላቅ መከራም ረዳታችን ነው ።

ስለዚህ ምድር ብትነዋወጥ ፥

ተራሮችም ወደ ባሕር ልብ ቢወሰዱ ፤ አንፈራም ።

መዝ ( 46 ) ፥ 1 - 2

ቁጥር አራት

# ከወንጌል ጥቂት

## በእጅዎ ያለዉ ወንጌል

" በእግዚአብሔር የታመነ ፤
እምነቱም እግዚአብሔር የሆነ ሰው ብሩክ ነው ። "

ኤር 17 ፥ 7

" በእርሱ የታመኑ ሁሉ የተመሰገኑ ናቸው ። "

መዝ 2 ፥ 12

" እርሱን በመተማመን የሚጠባበቁ ሁሉ
ብፁዓን ናቸው ። "

ኢሳ 30 ፥ 18

" እግዚአብሔር ቸር እንደሆነ ቅመሱ እዩም
በእርሱ የሚታመን ሰው ምስጉን ነዉ ። "

መዝ ( 34 ) ፥ 8

" በእግዚአብሔር የታመነ ምስጉን ነው ። "

ምሳሌ 16 ፥ 20

የእርስዎ መታመኛ ማነው ?

ልብ ይበሉ !

" የእግዚአብሔር ስም የፀና ግንብ ነው
ጻድቅ ወደ እርሱ ሮጦ ከፍ ከፍ ይላል ። "

ምሳሌ 18 ፥ 10

ይላል !

## በእጅዎ ያለው ወንጌል ።

## አወን ! እንነሳለን

ኤልያስ በሰራፕታ ያገለገለችውን ሴት ፤ ልጅዋን ከሞት አስነሳ፡-

1ነገ 17 ፥ 17 – 24

ኤልሳዕ የሱነማይቱን ሴት ፤ ልጅዋን ከሞት አስነሳ፡- 2 ነገ 4 ፥ 32

የኤልሳዕን የሞተ አጥንት ነክቶ የሞተው ከሞት ተነሳ፡- 2ነገ 13 ፥20-21

ጴጥሮስ ዶርቃን ከሞት አሳነሳ፡- የሐዋ 9 ፥ 36 – 41

ጳዉሎስ አውጤኪስ የተባለውን ወጣት ከሞት አሳነሳ፡- የሐዋ 20 ፥ 9

ኢየሱስ ናይን በምትባል ስፍራ የሞተውን ሰው አስነሳ፡-

ሉቃ 7 ፥ 11

ኢየሱስ የኢያኢሮስን ልጅ ከሞት አስነሳ፡- ሉቃ 8 ፥ 41-

ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት አስነሳ፡- ዮሃ 11 ፥ 1-44

ኢየሱስም ከሞት ተነሳ፡- ማቴ 28 ፥ 5 / ማር 16 ፥ 6

ኢየሱስ ሞትን ድል አድርጎ ሲነሳ ሞተው የነበሩ ብዙ ቅዱሳን ተነሱ፡-

ማቴ 27 ፥ 50 – 53

ዛሬ የተለዩን ወንድሞችና እህቶቻችንም እንዲሁ
በጌታ ቀን ይነሳሉ እኛም እናያቸዋለን ።
ለዚህ ህይወት ብቻ አልተጠራንም ። ለዘላለም ሕይወት እንጂ !
በዛ ሞት የለም ፤ ዕንባ የለም ፤ መለየትም የለም ። አወን !

አወን ! እኛም እንነሳለን

## ለንስሃ !

2ሳሙ 12 ÷ 1

" እግዚአብሔርም ናታንን ወደ ዳዊት ላከ ። "

ዝም ! ምንም እንዳልሆነ ። ፀጥ ! እረጭ ! ለአንድ ዓመት ያህል ። በውስጥ እሳት ቃጠሎ ፤ ሞት ፤ መንፈሳዊ ሞት ። እልህ ! ላለመስማማት ፤ ላለመመለስ ።

ንጉስ ዳዊት ፦ ከበግ እረኝነት ÷ የሕዝብ መሪነት ፤ በረከት ፤ ሁሉ የተሰጠው የሞላለት ዳዊት ፦ ዝም ! ኃጢያቱን ይዞ ፀጥ ለአንድ ዓመት ።

" ዝም ባልሁ ጊዜ አጥንቶቼ ተበላሹ ። " መዝ ( 32 ) ÷ 3
እያለ
ምነው ? ምነዉ ? ንስሃ አለመግባቱ ።

" እርጥበቴም ለበጋ ትኩሳት ተለወጠ ። " መዝ ( 32 ) ÷ 4
ደረኩኝ ፤ እንደድሮው የሕይወት ውሃ ምንጭ በሕይወቴ ሲፈስ አላየውም ከለምለምነት ወደ ድርቀት ሄጃለሁ ።

" በኃጢያተኛ ብዙ መቅሰፍት አለበት ። " መዝ ( 32 ) ÷ 10
የሚለው ዳዊት ምነው ? ለንስሃ አንድ ዓመት ፈጀበት ። ምነው ዝም አለ ? ኃጢያቱን ሸሸገ ፤ ሰወረ ።

መርጦታል ፤ ለይቶታል ፤ ወዶታልና ፦

" እግዚአብሔርም ናታንን ወደ ዳዊት ላከው ። "

ንስሃ እንዲገባ ፤ እንዲመለስ ፤ እግዚአብሔር ራሱ መልዕክተኛውን ላከለት ።
ወደ ሕብረቱ መልሶ ጠራው። እግዚአብሔር እርምጃን ወሰደ ።
ዳዊትን ፈለገ ፡ አይገርምም ? እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ለእርስዎም እንዲሁ ነው ። ግድ ይለዋል ፤
ወደ ሕብረቱም ይጠራዎታል ። በንስሃ ቢመለሱ ይምሮታል ።

ምናልባት እንደ ናታን ይህን መልዕክት ለእርስዎ ልኮት ይሆን ?
ለ-ን-ስ-ሃ- !

" ኃጢያት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን ÷
እዉነትም በእኛ ውስጥ የለም ። " 1ዮሃ 1 ÷ 8

## ወዴት ነህ ?

ዘፍ 3 ÷ 9

" እግዚአብሔር አምላክም አዳምን ጠርቶ ፦ ወዴት ነህ ? " አለው ።

እግዚአብሔር ራሱ በመልኩ የፈጠረውን ሰው ፤ የወደደውንና ያከበረውን ሰው በገነት አኖረው ። ይጠብቃትና ይንከባከባት ዘንድ ስልጣንን ሰጠው ።

ሰው ግን ÷ ያለ እግዚአብሔር እንደ እግዚአብሔር መሆን ፈለገና ፤ በእግዚአብሔር ላይ አመፀ ÷ ሄደ ፤ ትዕዛዝን ጣሰ፤ ወጣ

ድንገት ግልፅ ሲል ፤ ማንነቱን ሲያየው ፤ እርሱነቱን በእርሱነቱ ሲመለከተው ፤ ሲያስተውለው ፤ ለካስ እራቁት ነው ። ሕፍረት ነው ። ያለ አምላኩ ባዶ ነው ፤ ማፈሪያ ነው ።

ተሸሸገ ፤ ተሰወረ ፤ ለብሶ ተራቆተ ። አዳም !

እግዚአብሔር አምላክም አዳምን ጠርቶ ፦

የት ነበርክ ? አላለውም -----የት እንደነበረ ያውቃልና

ምን ሰራህ ? አላለውም------ምን እንደሰራ ያውቃልና

ምን አረክ ? አላለውም------ምን እንዳደረገ ያውቃልና

" ወዴት ነህ ? " አለው ------አሁን ባለህበት ሁኔታ
ወዴት ነህ ?

አውቃለሁ ! የተራቆትህ ነህ --ግን
ወዴት ነህ ።

ድምፅህን አሰማኝ ፤ መድሃኒት ልሁንህ ÷
ወዴት ነህ ?

በራቁትነት ፤ ከነኃጢያት ፤ ከነበደልህ ወዴት ነህ ?
ኢየሱስ ዛሬም ይፈልግሃል ፤ ድምፅህን አሰማኝ ይልሃል ወዴት ነህ ?

# ባለ ጫማ

**ዘፀ** 3 ፥ 5

" እግዚአብሔርም ሙሴን ጠርቶ ፦ አንተ የቆምህባት ስፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና ጫማህን ከእግርህ አውጣ ። "

አርባ አመት በፈረኦን ቤት ( የሐዋ 7 ፥ 22 ) የግብፅን ጥበብ ሁሉ ተማረ ፥ በቃሉም በስራውም የበረታ ሆነ ። ብንባልም

ታላቁን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመምራት እግዚአብሔር የራሱ ትምህርት ቤት አለውና ሙሴ ወደ ምድያም ምድር ተወስዶ አርባ አመት አሳለፈ ።

አርባ አመት ፥ ረጅም ጊዜ ፤ ረጅም ወቅት አለፈና እግዚአብሔር ድንገት በቁጥቃጦ ተገለፀለት ። ጫ-ማ-ህ-ን አ-ው-ል-ቅ !

ሙሴ ምን ያህል በፈረኦን ቤት የግብፅን ጥበብ ይማር እንጂ ፤ ምን ያህል በቃልና በስራዉ የበረታ ይሁን እንጂ ፤ በታላቁና በተፈራዉ ፤ በአብርሃም በይስሃቅና በያዕቆብ አምላክ ፊት ጫማን ማውለቅ ያላወቀ ሰው ነበር ።

" እግዚአብሔርም ሙሴን ጠርቶ ፦ አንተ የቆምህባት ስፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና ጫ-ማ-ህ-ን ከ-እ-ግ-ር-ህ አ-ው-ጣ ። " አለዉ ።

ሙሴ የሰማንያ አመት ሰው በነበረ ጊዜ እግዚአብሔር ጫማ ማዉለቅን ይማር ዘንድ ግድ ካለው እኛንማ ምን ያህል ?

ጫማ ከማስወለቅ በፊት ፤ ማውለቅ
ከመቀደስ በፊት ፤ መቀደስ
ከመባረክ በፊት ፤ መባረክ

ባለጫማ የትም አያደርስምና ከሙሴ ትምሕርትን ብንቀስም ደግ ነው ።

እርስዎ ምን ይላሉ ?

# እወስዳችኋለሁ !

**ዮሃ** 12 ፥ 24

" እውነት ፤ እውነት እላችኋለሁ ፥ የስንዴ ቅንጣት በምድር ወድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች ። ብትሞት ግን ፍሬ ታፈራለች ። "

እኔ ፤ እርስዎ -- ማንኛችንም ብንሆን ላለመሞት የማናደርገው ጥረት ፤ የማናባክነው ገንዘብና ጉልበት የለም ።

መኖር ( ሕይወት ) መልካም ነውና እንጥራለን ፤ እንደክማለን ለረዘመ እድሜ ፥ ለተትረፈረፈ ።

የእግዚአብሔር ቃል ደግሞ ካልሞትን በሕይወት እንደማንኖር ፍሬም እንደማናፈራ ይገልፅልናል ።

ዘር ሲዘራ ፥ ዘሩ ይቀበርና ይበሰብሳል ፤ ይረሳል----
ነገር ግን ወቅቱን ጠብቆ ፤ አሽቶ ፤ ( እሸት አዉጥቶ ) ወዝቶና በዝቶ ይነሳል ፤ ይመጣል ፤ ይታያል ።

እኛ መለየት ይታየናል------አምላካችን መሰብሰብ

እኛ መጉደል ይታየናል------አምላካችን መሙላት

እኛ ማነስ ይታየናል-------አምላካችን መብዛት

የምንወደውን በምድር ስንቀብረዉ ፥ በገነት ይነሳል ።

በዚህ ስንወድቅ------------በዛ እንነሳለን

" ፃድቃን ይሞታሉ ፤
ይህን ግን ማንም ልብ አይልም
ለእግዚአብሔር ያደሩ ሰዎች <u>ይወሰዳሉ</u>
ፃድቃን ከክፉ ይድኑ ዘንድ
<u>መወሰዳቸዉን</u> ማንም አያስተዉልም ። "

ኢሳ 57 ፥ 1 ( ትርጉም )

ሁላችንም እንሄዳለን ፤ እንወሰዳለን ለተሻለ ኑሮ ፥ ለሚበልጥ ክብር ለዘላለም ሕይወት ።

በዚህ እንፅናናለን ! እንበረታማለን ! አወን ! እንወሰዳለን ።

# <u>ተራራው</u>

ዘፍ 19 ፥ 17

“ እንዳትጠፋ ወደ <u>ተራራው</u> ሸሽተህ አምልጥ ። ”

ከፍ ያደርጋል ፤ ያላየነውን እንድናይ ፤ ያልደረስንበትን እንድንደርስበት ፤ ያላስተዋልነውን እንድናስተውል ያደርጋል ተራራ መልካም ነው ተራራ ።

እግዚአብሔር አብርሃምን በሞሪያም ተራራ ናና አምልከኝ አለው ። ዘፍ 22 ፥ 2 ተራራ ለዐምልኮ መልካም ነው ።

እግዚአብሔር የእስራኤል ልጆችን በሲና ተራራ ኑና መመሪያ ተቀበሉ አላቸው ። ዘፀ 19 ፥ 1- ተራራ ለመመሪያ መልካም ነው ።

እግዚአብሔር ሙሴን የተስፋይቱን ምድር እንዲያይ ወደ ፈስጋ ተራራ ና አለው ። ዘዳ 34 ፥ 1- ተራራ ለእይታ ጥሩ ነው ።

ኤልያስ በቀርሜሎስ ተራራ የበዐል ነብያትን ሁሉ ሰብስቦ የአምላኩን እውነተኛ አምላክነት አስመሰከረ 1 ነገ 18 ፥ 19
ተራራ የጌታን ስራ ሕዝብ ሁሉ እንዲያይ ለማድረግ መልካም ነው ።

ጴጥሮስ ፤ ያዕቆብና ዮሃንስ በመገለፅ ተራራ የጌታቸውን ክብር አዩ ማቴ 17 ፥ 1-8 ተራራ መልካም ነው የጌታን ክብር ለማየት ።

ነገር ግን ፥ ለደሕንነት የሚሆን ፤ በመከራ ሰዐት ሊያድነን የሚችል ተራራ ፤ ልንሸሽበት ፤ ልንሸሸግበት የሚገባ ተራራ ፤
የሁሉም ዐይኖች ሊያርፉበት የሚገባ ተራራ -

ብቸኛ ተራራ ፤ ጌታ በደላችንን የወሰደባት ተራራ ፤
ሃጢያታችን የተወገደባት ተራራ ፤
ተስፋን የሚያለመልም ተራራ

<u>የቀራንዮ ተራራ</u> ፤

<u>“ እንዳትጠፋ ወደ ተራራዉ ሸሽተህ አምልጥ !!! ”</u>

# <u>እንደ አይኖቻችን ትሆንልናለህ</u>

ዘሁ 10 ፥ 31

“ ከእኛ ጋር ና ፥ መልካም እናደርግልሃለን ! ” ዘፀ 10 ፥ 29
ሌላ ነገር ሲሆን ፤ “ እንደ አይን ትሆንልናለህ ” ደግሞ ለየትያለ ነገር ነውና ሊያጠያይቀን ይገባል ።

የግብፅን ምድር እንዲለቁ ያደረጋቸው ፤ እነዛን ታላላቅ ተአምራት በማድረግ ሞገስንና ክብርን የሰጣቸው ፤

“ በቀንና በለሊትም ይሄዱ ዘንድ መንገድን ሊያሳያቸው ቀን በደመና አምድ ፥ ሊያበራላቸውም ለሊት በእሳት አምድ እግዚአብሔር በፊታቸው ሄደ ። የደመና አምድ በቀን ፥ የእሳት አምድ በለሊት ከሕዝቡ ፊት ከቶ ፈቀቅ አላለም ። ” ዘፀ 13 ፥ 21

የተባለለት እግዚአብሔር የት ሄዶ ነው ? ሙሴ ! አወን ሙሴ ምድያማዊ ሰው እንዲመራው መለመኑ ? ምነው ? ሙሴ ምን ሆኖ ነው? እግዚአብሔርን እንዴት እረስቶ ነው ? በሰው ሊመራ የወደደዉ ፤ ምነው ?

ሙሴ ፡- በተሳሳተበት መንገድ እንዳትሳሳት ፤ በሳተበት መንገድ እንዳትስት ፤ ሕዝብዋን ወደ ክርስቶስ መንግስት እየመራች ያለችው የዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን ጥንቃቄ ታደርግ ዘንድ ለትምህርት ተፅፎልን ይሆን ?

“ በእናንተ መልካምን ስራ የጀመረው እስከ ኢየሱስ ክርስቶን ቀን ድረስ እንዲፈፅመው ይህን ተረድቼአለሁ ። ” ፊሊ 1 ፥ 6

አወን ! ከጀመረ የሚጨርሰው ፥ ከመራ የሚያደርሰው እርሱ ብቻ ነውና በእርሱ በእግዚአብሔር መንፈስ እንመራ እንጂ ፤ በሰው እዉቀትና ጥበብ አጉል መንገድ እንዳንጀምር ጠንቀቅ ነው ።

አይመስሎትም ?

# <u>ጥቂት ቀን</u>

ዘፍ 27 ፥ 44

ርብቃ ! ያንን የምትወደውን ፣ ከጉያዋ እንዲርቅ የማትመኘውን ፣ ተወዳጅ ልጅዋን ያዕቆብን በልብዋ እንዳሰበችው ፣ ይሆናል ብላ እንደገመተችው " ለጥቂት ቀን " ወደ ወንድምዋ ቤት ሰደደችው ።

" ጥቂት ቀን ! " ጥቂት ሳይሆን ፣ ያሰበችው ሳይሳካ ፣ የተለመችው ሳይከወን ፣ ያዕቆብ ሃያ አመት ያህል በላባ ቤት ማሳለፉ ያችን ባለ ምኞት ፣ ምኞት ብቻ አድርጓት ማለፉ እንዴት ያሳዝናል ።

" ጥቂት ቀን ! " ከዚያም ልኬ አስመጣሃለሁ ። ምኞት አልሰመረም ፣ አልሆነም ፣ ርብቃ ያዕቆብን ሳታየው አንቀላፋች ፣ በሞት ተወሰደች ።

ያሰበችዉ አልሆነም ፣ የተመኘችው አልደረሰም ፣ አይ ሰው ! ደርሶ ምኞት ብቻ ፡ ነገውን ሳያዉቀው ምኞት----ምኞት----ምኞት

" ጥቂት ቀን ! " ስንት ነው ? " ጥቂት ቀን " ከቤት ለመውጣት ፥ ለመሄድ ፣ ለመሸሽ ፣ ዘወር ለማለት ከሕብረት " ጥቂት ቀን " ምን ያህል ነው ? " ጥቂት ቀን " ።

ውበታችን " ሕብረታችን " ከሆነ ለምን ትተኸን ትሄዳለህ ? ለጥቂትስ ቀን ትለየናለህ ? ያላንተ ካላመርን ፣ ምነው ትጨክናለህ ? ጥቂት ቀን እኮ " ሃያም " ይሆናል ። አሊያም -------- ዘ-ላ-ለ-ም- ።

# <u>ቁጥቋጦ</u>

ዘፀ 3 ፥ 2

" የእግዚአብሔር መልአክ በእሳት ነበልባል ፣ <u>በእሾክ ቁጥቋጦ</u> መካከል ታየው "

ምነው ? ምነው ? ምነው በቁጥቋጦ ። በትንሽዋ ! ያውም በማትመቸው በምታሳምም በሾሃማ - ምነው ? ምነው ?

በቁጥቋጦ ! ምነው ? ዘለግላጋ ፣ የሚበቁ ለእይታ ፣ " ዛፎች " የት ሄደው ነው ? " ዋርካውና " " ፅዱ " ደግሞስ አቶ " ሾላ " የሚመቹ ለዚህ ስራ ምነው ለምን አልተመረጡ ምነው ?

ቁጥቋጦ ! ያውም የበረሃ ፥ ያልሰለጠነ ያልተገራ ተመረጠ ለዚህ ስራ ! ግሩም ! ግሩም ነው ! የእርሱ ስራ ፣ የመራጩ ----

ለዚህ ነውና !

1 ቆሮ 1 ፥ 26 " ወንድሞች ሆይ ፥ መጠራታችሁን ተመልከቱ ፣ እንደ ሰው ጥበብ ጥበበኞች የሆኑ ብዙዎች፥ ኀያላን የሆኑ ብዙዎች ፥ ባላባቶች የሆኑ ብዙዎች አልተጠሩም ። ነገር ግን እግዚአብሔር ጥበበኞችን እንዲያሳፍር የአለምን ሞኝ ነገር መረጠ ፣ ብርቱንም ነገር እንዲያሳፍር እግዚአብሔር የአለምን ደካማ ነገር መረጠ ። " ------ የሚለን ?

በበረሃ ቁጥቋጦ ከተጠቀመ -------በኔማ ? ----------- በልጁ ደም በተዋጀሁትና የልጅነትን ስልጣን በተቀበልኩት ምነው ? ምነው ? አይጠቀም ፥ እኔ እሺ ልበል እንጂ ፥ ራሴን ልስጠው እንጂ --

እግዚአብሔር ፦ ለታይታ የማይበቃዉን ቁጥቋጦ ፣ እንዲታይ የሚጎዳውን እሾሃማ ቁጥቋጦ ፣ የሚጠቅም ፥ ደካማን ብርቱ ካደረገዉ ፦ በእኔና በእርስዎም ይጠቀማልና ----እሺ እንበለዉ ፣ እንመቸው

አ-ይ-መ-ስ-ሎ-ት-ም

# ዕራቁት

ዘፍ 3 ÷ 7

“ እነርሱም ዕራቁታቸዉን እንደሆኑ አወቁ ። ”

ገነት ! በሰው ሳይሆን በእግዚአብሔር የተሰራች
“ እግዚአብሔር አምላክም ለማየት ደስ የሚያሰኘውን ÷ ለመብላትም መልካም የሆነውን የምድር ዛፍ ሁሉ የተከለባት ገነት ” ዘፍ 2 ÷ 9

ገነት ! የፍጥረት ሁሉ ተስፋ ፤ የጉዞአችን መደምደሚያ ÷ መቋጫ ሄደን የምናርፍባት ፤ እንባ ÷ ሃዘናችንን ረስተን ሃሴት የምንለብስባት ገነት ! እንባችንን ታብሰን ፤ እልል የምንልባት ÷ ቁስላችንን ታክመን በሆታ የምንወጣባት ገነት ።

በገነት ! በዛች በመልካሚቱ ስፍራ ፤ ሕፍረት በሚሸፈንባት በደል በሚወገድባት ፤ አዲስ ፍጥረት በሚኮንባት በዛች በገነት ዕራቁት ምነው ምነው ? ------------ዕ----ራ----ቁ----ት------

ለምን ? ለምን ልሸሽግ ? ለምንስ ልራቆት -----በገነት !----
መቼ አነሰኝ በምድር መሸሸጌ ፤ መሸማቀቅ መዋረዴ ፤ ለብሼ መራቆቴ

ለምን ? በገነት ዕራቁት ! ለምን ? እኮ ለምን ?

# አንደበት

2ሳሙ 16 ÷ 5-14

ምን ያህል ሃያላን ቢከቡዎ ፤ ጎበዞች ቢያጅቡዎ ፤ ዘመን ይመጣል ያልጠበቁት ! ለውርደትና ለሃፍረት የሚዳርግ ።

ከሩቅ ሳይሆን ከቅርብ ÷ ከባዳ ሳይሆን ከወዳጅ ድንገት አንዱ ይነሳና ባለ አንደበት ይሆንብዎታል ። አመድ ይረጫል ፤ ድንጋይ ይወረውራል ። ዘመን ነውና --------እርስዎም ዝም------------

ሳሚ የተባለው ይህ ሰውም ÷ በዳዊት ላይ ድንጋይ ወረወረ ትቢያንም ነሰነሰ ። እርግማኑንም ሰነዘረ ።

ሊበቀለው አልወደደም ዳዊት ÷ ተውት አለ ። ዘመን ነውና ይሁን አለ ። ጨመረ ፤ ጨመረ ፤ አሁንም ፤ አሁንም ፤ በተነ ÷ ወረወረ መታቸው ፤ ሰደባቸው ፤ ሌላው ጦር መዘዘ ÷ ሰነዘረ አልቻለምና ፎከረ ግና ! ዳዊት ገሰፀው ፤ ተው አታድርግ አለው ፤ መከረው ።
ዘመን ነው አለው ።

አንደበት ! ክፉ ነው ። ጦር ይሻላል ጎራዴ ፤ አንደኛውን ገላግሌ ። ግን አንደበት ክፉ ነው ፤ ሃይለኛ ነው ።

“ አንደበት እሳት ነው አንደበት በብልቶቻችን መካከል ዓመፀኛ አለም ሆኖአል ። ስጋን ሁሉ ያሳድፋልና ። ”( ያዕ 3 ÷ 6 )

ደግሞ ከውርደት ሲነሱ ፤ ሲታሰቡና ሲጎበኙ ፤ ዘመን ሲመጣ ለእርስዎ ( 2 ሳሙ 19 ÷ 15 - 22 ) ቀድሞ ይመጣል ለሙገሳ ፤ ( ቁ 20 ) ዳዊት ወደ ስልጣኑ ለመመለስ መንገድ ሲጀምር ለሙገሳ መጀመሪያ የመጣው ይሄው ሳሚ ነበር ፤ አንደበት ! “ ክፉ ነዉ ሃይለኛ ( ያዕ 3 ÷ 8 ) ወላዋይ ። ”

እንዴት ልቋቋመው ? እንዴት ላሸንፈው ? ይህን ሃይለኛ ። ዋ ! አንደበት ! ዋ ! በገፅታዬ ተሸፍኖ እኔን ያሳጣል ፤ ያዋርዳል የኔው አንደበት ።

የ-እ-ር-ስ-ዎ-ስ ?

# <u>አቀበት</u>

2ሳሙ 15 ÷ 30

“ ዳዊትም ተከናንቦ ያለ ጫማ እያለቀሰ ወደ ደብረ ዘይት <u>ዐቀበት ወጣ</u> ”

በገዛ ልጁ ! ተገፋ ፤ ተባረረ ። ቤተ መንግስቱንና የሚወደውን በስሙ የተሰየመውን የዳዊትን ከተማ ኢየሩሳሌምን ለቀቀ ፤ ሄደ ፤ ወጣ በእንባ ፤ በለቅሶና በውርደት ራሱን ተከናንቦ ያለ ጫማ ሄደ ፤ በፍጥነት ነጎደ

ምኞቱና ፀሎቱ አልሰመረም ------------

“ እግዚአብሔርን አንዲት ነገር ለመንሁት ÷ እርስዋንም እሻለሁ ፤ በሕይወት ዘመኔ ሁሉ በቤቱ እኖር ዘንድ ÷ መቅደሱንም እመለከት ዘንድ ” ያለው ። ከቤተ መቅደሱ መገኛ ዉጭ ሕይወት የለኝም ያለው መና ሆነ ፤

እንደ እግዚአብሔር ልብ የሆነ ዳዊት ÷ የእግዚአብሔር ቅባት በላዩ ያለ ዳዊት ÷ በእግዚአብሔር እንጂ በሰው ያልተመረጠ ዳዊት ፦

ወንድ ልጅ ሊያደርገው በማይገባው ሁኔታ ተከናንቦ ፤ ያለ ጫማ እያለቀሰ ከሚወዳት ከኢየሩሳሌም ከእግዚአብሔር ታቦት መቀመጫ ይውጣ እንጂ ይሄድ የነበረው ወደ ደብረ ዘይት <u>አቀበት</u> ነበር ።

ወደ አቀበት ፤ ወደ ላይ ፤ የሚያነሳ መከራ ፤ የእግዚአብሔርን ማንነት ከመቸውም ጊዜ ይልቅ ሊያሳየን ያለ መከራ አቀበት እንጂ ቁልቁል የማያስኬድ መከራ ።  ዳዊት ያለፈበት

በደሙ ተዋጅተው ÷ መገለፁን እየተጠባበቁ ያሉት ፤ በመንፈስ ቅዱስ ታትመዉ የልጅነትን ስልጣን የተቀበሉት ልጆቹ የሚያልፉበት መከራ  ከፍ ሊያደርግ ወደ አቀበት ሊያወጣ እንጂ ማንንም ወደታች ፤ ወደ ቁልቁለት የማያወርድ አለ መሆኑን ልንማርበት ለጥቅማችን  የዳዊት እያንዳንዱ ጉዞ ተፃፈልን ።

እርስዎ አሁን ያሉበት መከራና ጭንቀት ወዴት እየወሰደዎ ነው ??

አቀበት ! ወይስ ? ቁልቁለት !

# <u>ምነው</u> ?

ዘፍ 9 ÷ 20

“ ኖሕም ገበሬ መሆን ጀመረ ÷ ወይንም ተከለ ።
ከወይን ጠጁም ጠጣና ሰከረ ። በድንኳኑም ውስጥ ዕራቁቱን ሆነ ። ”

በጠራራ ፀሃይ ፤ ዝናብ ባልታየበት ዘመን ፤ በእምነት መርከብን ያዘጋጀው ኖሕ ፤ የሕዝቡን ዝልፊያና አሽሙር የተቋቋመዉ  ኖሕ ፤

ዕብ 11 ÷ 7   “ ኖሕ ገና ስለማይታየው ነገር ተረድቶ እግዚአብሔርን እየፈራ ቤተ ሰዎቹን ለማዳን መርከብን በእምነት አዘጋጀ በዚህም አለምን ኮነነ ÷ በእምነትም የሚገኘውን ፅድቅ ወራሽ ሆነ ። ” የተባለለት ኖሕ ።

ከጥፋት ውሃ በኋላ ለአምላኩ መስዋዕትን ( ዘፍ 8 ÷ 20 ) ያቀረበና መስዋዕቱም ተቀባይነትን ያገኘለት ኖሕ ፤ ያንን ታላቅ መከራ ፤ የጥፋትን ውሃ ያክል ጭንቅ እግዚአብሔር የከለለው ኖሕ ------ ምነው ? ምነው ?

ምነው ? ያ ሁሉ እምነትና በአምላክ መደገፍ ÷ ያ ሁሉ ለአምላክ መለየት ፤ ምነው የት ? ኧረ የት  ሄዶ ነው ? ለወይን ጠጅ ራሱን እንዲህ <u>በፍጥነት</u> መስጠቱ ራሱን ማዋረዱ ? መራቆቱ ?

ለምን ፈጥነን እንራቆታለን ?  እንዋረዳለን ? እግዚአብሔር በኛ መስራት ከመጀመሩ ፤ የፅድቅን ሸማ ከመልበሳችን ፈጥነን ለምን ራቁት እንገኛለን ? ከመንፈስ ይልቅ በወይን ጠጅ እንሰክራለን ?   ኧረ ምነው ?

ለምን ከክብረት ውርደት ! ከከፍታ ዝቅታ ! ከመንፈሳዊ ስጋዊ ! ኧረ ምነው ? ምነው ይቀናናል ? ምነው ? አይገርምም ? ከክብረታችን ውርደታችን መቅደሙ ?

እግዚአብሔር በእኛ ያደረገውን መልካም ነገር መስክረን ሳንጨርስ ውርደት ÷ ራቁትነት ÷ ባዶነት -------- ምነው ? ምነው ?

“  ለራስህና ለትምሕርትህ  ተጠንቀቅ ! ”   1ጢሞ 4 ÷ 16

# እንባ

ዘፍ 21 ፥ 16--------አጋር ቃልዋን አሰምታ አለቀሰች
ዘፍ 27 ፥ 38 -------ኤሳው ቃሉን አንስቶ አለቀሰ
ዘፍ 29 ፥ 11 -------ያዕቆብ ቃሉን ከፍ አድርጎ አለቀሰ
ዘፍ 33 ፥ 30 -------ዮሴፍ ወደ እልፍኝ ገብቶ ከዚያ አለቀሰ
ዘፍ 45 ፥ 14 -------ብንያም በዮሴፍ አንገት ላይ አለቀሰ

ዘፀ 2 ፥ 6 -------ሙሴ ያለቅስ ነበር

ዘሁ 11 ፥ 10 -------የእስራኤል ሕዝቦች አለቀሱ

ሩት 1 ፥14 ---------ኦርፋና ሩት አለቀሱ

1ሳሙ 1 ፥ 8 -------ሃና አለቀሰች
1ሳሙ 24 ፥ 16 ----ሳኦልም ድምፁን ከፍ አድርጎ አለቀሰ

2ሳሙ 13 ፥ 36 ----ዳዊትና ልጆቹ ድምፃቸዉን ከፍ አድርገዉ እጅግ ታላቅ ለቅሶ አለቀሱ

2ነገ 8 ፥ 11 --------ነቢዩ ኤልሳ አለቀሰ
2ነገ 20 ፥ 3 ------- ሕዝቅያስ እጅግ አድርጎ አለቀሰ

ዕዝ 10 ፥ 1 --------ዕዝራ አለቀሰ

ነሕ 1 ፥ 4----------ነሕምያ ተቀምጦ አለቀሰ

ኢሳ 22 ፥ 4 -------ስለ ሕዝቤ ጥፋት መራራ ልቅሶ አለቅሳለሁ

ሰቆ. ኤር 2 ፥ 11----አይኔ በእንባ ደከመች ፤ አንጀቴም ታወከ

ኢዮ 2 ፥ 12--------የኢዮብ ጓዶኞች ስለ ኢዮብ አለቀሱ
ኢዮብ 16 ፥ 20-----በእግዚአብሔር ፊት እንባ አፈሰሰ

ማቴ 26 ፥ 75 ------ጴጥሮስ መራራ ልቅሶ አለቀሰ

ማር 16 ፥ 10 ------ደቀ መዛሙርቱ አለቀሱ

የሃዋ 20 ፥ 18 ------ጳዉሎስ አለቀሰ

2 ጢሞ 1 ፥ 4 ------ጢሞቲዎስ አለቀሰ

ራዕ 5 ፥ 4 ----------ዮሃንስ አለቀሰ

## ባለ እንባ ነዎት ?

እነዚህና ሌሎችም አያሌ ወንድሞችና እህቶች በየጊዜው እንባቸውን በሕያው አምላካቸው ፊት ከእርስዎ ጋር አፍስሰዋል ። ዛሬም በየስፍራው አያሌ እንባዎች ይፈሳሉ ። ወደ ፊትም !

ዮሃ 11 ፤ 35 --------“ ኢየሱስም እንባውን አፈሰሰ ” የሚለውን ሲያነቡ ምን አሉ ?

አወን ብቻዎን አይደሉም ! እንባ በዚህ ፤ እንባ በዚያ እንባ ! እንባ ! እንባ !

እስከ--------- ራዕይ 7 ፥ 17 “ በዙፋኑ መካከል ያለዉ በጉ እረኛቸዉ ይሆናልና ፥ ወደ ሕይወትም ውሃ ምንጭ ይመራቸዋልና ፥ እግዚአብሔርም እንባዎችን ሁሉ ከአይናቸዉ ያብሳል ። ” አሜን !

አይዘገይም ! ይመጣል ! እንባንም ያብሳል !

# መልካም አይደለም !

ዘፀ 18 ፥ 17

የሙሴም አማት አለው :- " አንተ የምታደርገዉ ይህ ነገር መልካም አይደለም ! "

በፍፁም ! ስላላወቀ ነው አትበለኝ ፤ ያውቃልና ::
ስላልደረሰበትም ነው አትበለኝ ፤ ደርሶበት ወስኖበታልና ::
ሂድ ! ሂድና ዘፀ 17 ፥ 8 ጀምሮ ተመልከት :-

ሙሴ ! ሙሴ ራሱ ከአማሌቅ ጋር ሊዋጋ ባለ ጊዜ ኢያሱን ጠርቶ " ጎልማሶች ምረጥልንና ወጥተህ ከአማሌቅ ጋር ተዋጋልን " ብሎ አዘዘዉ. ጎልማሶችን ምረጥልን :- ምክንያቱም አሉና ::
ጎበዞችን ፤ ለውጊያ የሚሆኑትን ምረጥልን :- ምክንያቱም በመካከላችን አሉና

ሙሴ :- አካባቢውን መመልከት የሚያውቅ ሰው ነው ፤ አወን " ሙሴም:- የግብፆችን ጥበብ ሁሉ ተማረ ፥ በቃሉም በስራዉም የበረታ ሆነ የሐዋ 7 ፥ 22 ስለሚለን ፤ ሙሴ ስራን ለሰራተኛ መስጠት ምን ያህል ፍሬአማ እንደሆነ ከማንም የበለጠ ያዉቃል ::

ታዲያ ምን ነው ? ምነዉ ሙሴ ብዙ ሸክም ብዙ ጫና በራሱ ላይ አደረገ ? ከጠዋት እስከ ማታ እርሱ ተቀምጦ ሕዝብን አቆመ :: ምነው ? ከውጭ መካሪ ፈለገ ? ይ-ህ-----የ-ም-ታ-ደ-ር-ገ-ዉ-----መ-ል-ካ-ም አ-ይ-ደ-ለ-ም !!!

ማን ይደፍራል ይህንን ለማለት ፤ መሪን ለመገሰፅ ፤ ለመምከርና ለማስተካከል :: ስራ እንዳይበደል ማን ይቆረቆራል ? እኔ ? እርስዎ ? ማን ?

የሺህ አለቆች ፥ የመቶ አለቆች ፥ የአምሳ አለቆችና የአስር አለቆች እግዚአብሔርን የሚፈሩና የታመኑ በእርስዎ አካባቢ ሞልተዋልና ተነሱ ሹሙላቸዉ ፤ አወን እግዚአብሔርን የሚፈሩ :- እነርሱ ሁልጊዜ በመካከላችን አሉና እግዚአብሔር መንፈሳዊ አይኖችዎን ያብራልዎ !

ይህ የሚያደርጉት መልካም አይደለምና !

# መድረኩ ! ( ፑልፒቱ )

ነህምያ 8 ፥ 5

" ዕዝራም :- በሕዝቡ ሁሉ ላይ ከፍ ብሎ ፤ ሕዝቡ ሁሉ እያዩ መፅሃፉን ገለጠ ፥ በገለጠም ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ ቆሙ :: "

" ዕዝራም :- ስለዚህ ነገር በተሰራዉ በእንጨት መረባረብ ላይ ቆሞ የህጉን መፅሃፍ ፥ ከማለዳ እስከ ቀትር ድረስ አነበበዉ :: "
8 ፥ 3

ከሕዝቡ በላይ ከፍ ብሎ የተሰራው መረባረብ ( መድረክ ) በዕዝራና በሕዝቡ መካከል መለያየትን አድርጎ ዕዝራ ከፍ እንዲል ፤ ሕዝቡ ግን ዝቅ ብሎ ዕዝራን ቀና ብሎ እንዲመለከት ሳይሆን :-

የእግዚአብሔር ቃል ከሁሉም ከፍ ያለ መሆኑን ለማሳየት ፤ ወንጌሉን በአደራ ተቀብሎ የሚያስተምረውም ፤ የሚሰማውም ከወንጌሉ ስር እንጂ ማንም የበላይ አለመኖሩን እንድናውቅ ነው :-

ነህ 8 ፥ 4 " ፀሃፊውም ዕዝራ ስለዚህ ነገር በተሰራው በእንጨት መረባረብ ላይ ቆሞ ነበር :: " የሚለን :: ስለ ወንጌሉ የተሰራ ከፍ ያለ መረባረብ እንጂ ባለፑልፒቱን ለማግነን ወይም ከፍ ለማድረግና አድማጩን ከስሩ እንዲያይ ስላልሆነ ጥንቃቄ ያሻል ?

ይህም ከፍ ያለው ስፍራ ( መድረክ ወይም ፑልፒት ) በራሱ ተራ የእንጨት መረባረብ እንጂ ምንም ሌላ ባለመሆኑ ፤ በፍፁም የተለየ አክብሮትን እንዳንሰጠው ልንጠነቀቅ ሲገባ ፥ ካከበርን :- ኢየሱስ የሞተለትን ፤ በደሙ የተዋጀውን " ወንድም " ወይም " እህት " ይሁን እንላለን ::

እርስዎ ምን ይላሉ ?